# የዘር ማጥፋት ወንጀል /Crime of Genocide/ ምን ማለት ነዉ? ሊወሰዱ የሚገባቸዉ ቅድመ ጥንቃቄዎችስ ምንድን ናቸዉ?

ሸንቁጥ አየለ

August 5, 2017

እስካሁን በሰዉ ልጅ የታሪክ ሂደት ዉስጥ የአለም ማህበረሰብን የፈተኑ በርካታ ታሪካዊ አጋጣሚዎች (ጦርነት: ርሃብ: ስደት: በሽታ: በአምባገነንነት የተነሳ የሚከሰት ጭቆና: በህግ አልባነት የሚከሰት ጭቆና) ቢኖሩም ከሁሉም ፈታኝ ሁኔታዎች ግን መራራ የማህበረሰባዊ ስብራት በማስከተልና በትዉልድም ልብ ዉስጥ የማይሽር ቁርሾን በመከተብ የሚታወቀዉ አንድ ማህበረሰብ ወደ ፍጹም ህግ አልባነት ሁኔታ ዉስጥ በሚገባበት ጊዜ ተያይዞ የሚከተለዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነዉ::

የዘር ማጥፋት ሲባል ለምሆኑ ምን ማለት ነዉ? የዘር ማጥፋት በተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ትርጉም ቢሰጠዉም በአለም አቀፍ ደርጃ በተባበሩት መንግስታት እንደ ኢሮፓዉያን አቆጣጠር በ 1948 ዓም በወጣዉ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ስለመከላከልና ስለመቅጣት የተደረገ ስምምምነት (Convention on the Prevention and Punishment of the Crime of Genocide) በሚለዉ ሰነድ በአንቀጽ 2 ስር በግልጽ ህጋዊ ትርጎሞች ተቀምጠዉለታል::

በዚህ አለም አቀፋዊ የህግ ትርጉም መሰረትም የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚባለዉ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱ ወይም በከፊል አልዚያም ሁሉም ሁኔታዎች ሲከሰቱ ነዉ:: ከላይ የተጠቀሰዉ ሰንደ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ሲተረጉም ማንኛዉም ድርጊት ሆን ተብሎ አንድን ሀገር /ብሄር/ዘር/ጎሳ/ሀይማኖት/ ቡድን በከፊል ወይም በሙሉ ለማጥፋት ተብሎ የሚደረግ ግድያ : በቡድኑ አባላት ላይ የሚደረግ የአካል ወይም የአዕምሮ ጥቃት : በቡድኑ አባላት የኑሮ ሁኔታ ላይ የሚሰነዘር ጥቃት : በከፊል ወይም በሙሉ በቡድኑ አባላት ላይ የፊዚካል ጥፋት ለማምጣት ተብሎ የሚደረግ ጥቃት: የዘር መተካታቸዉ እንዳይቀጥል ታስቦበትና ሆን ተብሎ የወሊድ መከላከል እርምጃ በማህበርሰቡ ላይ የተወሰደ እንደሆነ እንዲሁም የቡድኑን ህጻናት ወደ ሌላ ማህበረሰብ አባላት በሀይልና በጉልበት እንዲዛወሩ ከተደረገ በዘር ማጥፋት ወንጀል ሰር እንደሚወድቅ ያብራራል::

“any of the following acts committed with intent to destroy, in whole or in part, a national, ethnic, racial or religious group, as such: killing members of the group; causing serious bodily or mental harm to members of the group; deliberately inflicting on the group conditions of life, calculated to bring about its physical destruction in whole or in part; imposing measures intended to prevent births within the group; [and] forcibly transferring children of the group to another group.”

ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሰተ የሚባለዉ ግድያ ሲፈጽም ብቻ ሳይሆን የአንድ ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ሆን ተብሎ ጥቃት ስር ሲወድቅ ጭምር ነዉ::

የአንድ ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ሲባልም የቀየሳት ደሳሳ ጎጆ: ይተዳደርባት የነበረች የኑሮ ዘዴ ( ማለትም ግብርናም : ንግድም: ሸክምም ወይም ማንኛዉም ሞያ) ሲበጠበጥበት : ኑሮ መስርቶ ይኖርበት ከነበረዉ አካባቢ ማህበረሰብ ጋር የመሰረተዉ ማህበራዊ / ኢኮኖሚያዊ/መንፈሳዊ / ታሪካዊ ትሥስር ሁሉ ሲናጋበት እና በህግ የተደነገገለት ኑሮዉን በየትኛዉም የሀገሪቱ ክፍል ሊኖር እንደሚችል የሚያዉጀዉ የሙብት ክፍሉ ሲነጠቅ: ልጆቹ ሲማሩበት ከነበሩበት ትምህርት ቤት ትምህርታቸዉ ሲቋረጥ እና የስነልቦና ጫና ሲደርስባቸዉ : ከአንድ አካባቢ በሚደረግበት ተጽዕኖ ወደ ሌላ አካባቢ በሚያደርገዉ እንቅስቃሴ ሂደት ዉስጥ የሚደርስበት የስነልቦና / የአካል/ የሞራል እና የስሜት ስብራት እንዲሁም የሚገጥመዉ ርሃብ: ጥማት: የጤና መታወክ ሁሉ ግንዛቤ ዉስጥ ተካተዉ ነዉ:: የአንድ ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ሀብታም ወይም ድሃ መሆኑ ሳይሆን ግንዛቤ ዉስጥ የሚገባዉ ያ የተጠቃ ቡድን/ማህበረሰብ/ብሄረሰ/ጎሳ/የሀይማኖት ቡድን የደረሰብት ጉዳት የሚሰፈረዉ ከላይ የተባሉ ሁኔታዎችን ሁሉ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት ነዉ::

ከዚሁ የዘር ማጥፋት ወንጀል ትርጓሜ ሳንወጣ ትርጉሙን በማስፋት ሌላዉ ቀርቶ አንድ አመለካከት ያነገቡ የፖለቲካ ቡድኖችን/ፓርቲዎችን ማጥፋት እንኳን የዘር ማጥፋት ወንጀል ነዉ የሚል ሀሳቤን እስከማካተት የመራመድ አስተሳሰብ አለ:: ይሄንኑ አለም አቀፋዊ የህግ አስተሳሰብ በመከተልም የደርግ ባለስልጣናት ላይ ክስ ተመስርቶ በነበረበት ወቅት ደርጎቹ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽመዋል የሚለዉን ጭብጥ አጉልቶ ያወጣዉ ክርክር በተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች/ፓርቲዎች ላይ የወሰዱት የማጥፋት/የማጽዳት ስራ ጭምር እየተመዘዘ ነዉ:: እናም የዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሀሳቤ መሰረቱ ሰፊና በርካታ ጉዳዮችን የሚያካልል በመሆኑ ሀገራት በየደረጃዉ የሚያስቀምጧቸዉን የፖለቲካ አመራር አካላት በቂ ግንዛቤ ሊፈጥሩላቸዉ ይገባል:: በአሁኑ ወቅት ወያኔ የምትፈጽመዉ የፖለቲካ ቡድኖችን የማጥፋት እርምጃ ከደርጎቹ ያንስ ወይም ይበልጥ እንደሆነ ህግ ሚዛን ፊት ቀርብ የሚታይ ጉዳይ ይሆናል::

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበረሰቦች/ጎሳዎች/ሀይማኖቶች አመለካከት ያላቸዉ ቡድኖች በሚኖርበት ሀገር ዉስጥ በየደረጃዉ የሚገኙ ባለስልጣናት በዚሁ አለም አቀፍ ህግ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ስልጣነ መንበሩን የሚዘዉሩ ሀይሎች አበክረዉ እንዲሰሩ ይመከራሉ:: ይህ እንግዲህ ባለስልጣናቱ ስህተት የሚሰሩት ከእዉቀትና ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ ነዉ የሚለዉን ጠባብ ጭብጥ በማንጠልጠል የሚደረግ ትንታኔ መሆኑን ሳንዘነጋ ማለት ነዉ::

አንድን ማህበረሰብ/ብሄረሰብ 20 እና 30 አመት ከኖረበት አካባቢ ህገ መንግስታዊ መብታቸዉን በመግፈፍ በተዋረድ ደረጃ ባሉ የክልል ባለስልጣናት ካፈናቀሉና ካባረሩ ብሎም የኑሮ ሁኔታቸዉን ካቃወሱና ከበጠበጡ ብኋላ ያ ህበረሰብ/ብሄረሰብ የመብት ክስ ሲመሰርት የደረሰዉ በደል ለክስ አያበቃም ብሎ መልስ መስጠት ወይም ወደ አካባቢዉ የሄዱት ደን ሊጨፈጭፉ ነዉ ብሎ መመለስ ወይም ደግሞ ከአካባቢዉ የሸሹት ስለፈሩ ነዉ ብሎ መመለስ ወይም ደግሞ የተባረሩት ሰዎች ቁጥር እንደተባለዉ ብዙ አይደለም ብሎም ማደናገር ከላይ እስከታች ያሉ የሀገሪቱ ባለስልጣናት ዘንድ ስለ ዘር ማጥፋት ወንጀል የግንዛቤ እጥረት ስላለ በዚሁ ዙሪያ የሚመለከተዉ ወገን የግንዛቤ ማስጨበጥ መስራት ይገባዋል ብሎ ምክር መስጠቱ መልካም ነዉ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው::

ባለስልጣናት ግንዛቤአቸዉን ከፍ ለማድረግና ቀና ምክርን ተግበራዊ ለማድረግ በጎ ፈቃደኝነቱ ይኖራቸዋል የሚለዉን ተነጣይ ታሳቢ በመመርኮዝ ባለስልጣናት እዉቀታቸዉን ከፍ ያደርጉ ዘንድ መስራት ተገቢ ነዉ:: ከዚሁ አለም አቀፍ ህግ ጋርም በህገ መንግስቱ ስር በሰፋት የተደነገጉ ሰበአዊ መብቶችን አብሮ በብቃት በማጥናት ለተግባራዊነታቸዉ መትጋት ተመክሮ የሚታለፍ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በተዋረድ ላሉ ባለስልጣናት ግዴታም ጭምር መሆኑን ማሳሰብ ከባለ እምሮዎች ሁሉ ይጠበቃል::

አተገባበርና አፈጻጸሙ ላይ የሚያነሳቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች ቢኖሩም (ለምሳሌ የህጉ በነጋሪት ጋዜጣ መታተም) የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አለም አቀፍ ህጎችን ከመቀበሉ አንጻር ይሄንኑ የዘር ማጥፋት ወንጀል ህግ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እንዲሁም የሚመለከታቸዉ ሁሉ በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ ሊይዙበት ይገባል:: ባለስልጣናት የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነዉን ህገመንግስት ወደ መሬት ማዉረዱ ዋነኛ ስራቸዉ የመሆኑን ያህል አለም አቀፍ ህጎችንም በቅርበት ሊመረምሯቸዉና ተግባራዊ ሊያደርጓቸው እንደሚገባ ደጋግሞ መጮህ በሰበአዊ መብት ሙግት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ወገኖች ሁሉ ሳይታክቱ ሊተገብሩት የሚገባ አላማ ሲሆን መላዉ ማህበረሰብም ለራሱ ጥቅም ሲል ድምጹን ከፍ አድርጎ ሊዘምረዉ የሚገባ ጣፋጭ ሙዚቃዉ ሊሆን ይገባል::

ይሄንኑ የእዉቀትና ግንዛቤ ጉዳይ ተገንጣይ ታሳቢ በማድረግ በአንዲት ሀገር ዉስጥ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዳይከሰት ለመከላከል ምንም ምን ቅድመ ርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል የሚለዉን ጭብጥ የሚመለከታቸዉ ሁሉ (በተዋረድ ያሉ ባለስልጣናት : የሀገሪቱ ዜጎች: አጥቂና ተጠቂ ወገኖች : አለም አቀፍ ማህበረሰብ) ትኩረት እንዲያደርጉበት ማስቻል ይገባል:: ከሁሉ በፊት የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚጸነዉ በተሳሳተ አመለካከት ላይ የሚቆም አንድ ተወንጫፊ ግብ ያለዉ ሀይል ማህበረሰቡን በስህተት ሀሳቤ ሲበክለዉ ነዉ::

ሂደቱን የሚያፋጥነዉ ደግሞ ይሄንኑ ስህተት ሀሳቤ ያነገበዉ ሃይል በማህበረሰቡ ዉስጥ ያለዉ ጉልበትና ተሰሚነት በልዩ ልዩ መስክ (በኢኮኖሚ: ፖለቲካ: ማህበራዊ ዘርፍ) ጎልብቶ ሲዳብር ነዉ:: ከዚህ የከፋ የሚሆነዉ ደግሞ ይሄዉ ቡድን በአንድ ስርዓት ዉስጥ የበላይነት አስተሰሰብን ማስፈን የሚችልበት ደርጃ ላይ ሲደርስ ነዉ:: ይሄ ሁሉ ሁኔታ ከመከሰቱና ነገሮች ወደ ማይጨበጥ አዘቅት ዉስጥ ከመወርወራቸዉ በፊት ሁሉም ያገባኛል ባይ ሂደቱን በጥንቃቄ ሊገመግመዉና የተሳሳተ አስተሳሰብ አራማጅ ሀይሉ መሰረታዊ የሀይል ሚዛኑ የት ድርስ እንደሆነ መፈተሹ ተያያዥ መፍትሄዎችን

ለማሰስ ያግዛል::

በዘር ማጥፋት ሂደት ላይ ጥናት ያደረጉ እነ ግሬጎርይ ስታንቶን እንደሚተነተኑት የዘር ማጥፋት በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ ከመከሰቱ በሚፊት : በሂደቱ ወቅት እና ከሂደቱ ብኋላ የሚታዩ ክስተቶች አሉ ይላሉ:: እነዚህም እየተጠቃ ባለዉ ቡድን ላይ የሚከናወን ኢ ሰበአዊ አያያዝ : የአጥቂዎቹ ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀት : የዘር ማጥፋቱን ካከናወኑ ብኋላ ፈጽሞ የዘር ማጥፋት አልተከናወነም ብሎ አይኔን ግንባር ያድርገዉ ማለት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ ይላሉ:: እነዚህ ሁኔታዎች ሲስተዋሉ በሚመለከተዉ ወገን ሁሉ (በሃገሪቱ ባለስልጣናት :በየሀገሪቱ ዜጎች: በተጠቂ ወገኖች : በራሳቸዉ በአጥቂ ወገኖች : እንዲሁም በአለም አቀፍ ማህበረሰብ) እርምጃ መዉሰድ ካልተቻለ የጥፋቱ ግዝፈት ማለቂያም ማቆሚያም የለዉም ሲሉ ይመክራሉ::

/Gregory Stanton have postulated that conditions and acts that often occur before, during, and after genocide—such as dehumanization of victim groups, strong organization of genocidal groups, and denial of genocide by its perpetrators—can be identified and actions taken to stop genocides before they happen./

አዳምስ የሚባለዉ የዘር ማጥፋት ሂደት ተመራማሪ ደግሞ የዘር ማጥፋት የሚከሰተዉ ከድህነት: ከኋላቀርነት እንዲሁም ከኢኮኖም ድቀት ጋር ተያይዞ እንደሆን ያብራራል:: እሱ እንደሚለዉ በድህነት የሚማቅቅ ማህበረሰብ በሚኖርበት ጊዜ ኋላ ቀር የሆኑ ስልጣን ናፋቂ ቡድኖች ደጋፊ ለማግኘት የራሳቸዉን ማህበረሰብ/ጎሳ/ቡድን/የሀይማኖት ቡድን በጥላቻና በፍርሃት ይበክሉና ሌላ የሚሉትን ቡድን/ጎሳ/ብሄረሰብ ከምድረ ገጽ ለማስጠፋት አበክረዉ ይሰራሉ:: የራሳቸዉን ቡድን በስጋትና በጠባብነት ያጥሩታል:: ለዚህም አስተሳሰባቸዉ አንድ መጠቃትና መጥፋት ያለበት ቡድን ያበጁለትና በዚሁ አስተሳሰብ ዙሪያ ደጋፊ ያሰባስባሉ::በድህነት የታነቀ : በኋላቀርነት የተተበተብ : በጥላቻ የተወጠረ: የፈራ: የመኖር ህልዉናዉ የበረገገ ቡድን/ጎሳ/ማህበረሰብ/ብሄረሰብ ደግሞ የዘር ማጥፋት

ለማከናወን ከበቂ በላይ ዝግጁ ነዉ ይላል::

/ Adams :- “Genocides Roots in the Overpopulation Cycle, holds that genocide



occurs as unsustainable civilizations decline, suffering shocks that accompany economic earthquakes. Hungry, frightened, scared masses demand survival and reassurance. Opportunistic leaders may now benefit by sacrificing ‘others, outsiders’ for the sake of supporters in leaders’ quests for power and influence. Once overwhelming pains precondition our human overpopulation-violent psychology, genocidal explosions await what Adams called the “holocaustic spark.”

እንደ ኤሮፓዉያን አቆጣጠር በ 1996 እና በ 2012 ሬጎርይ ስታንቶን (የጀኖሳይድ ዋች ፕሬዝዳንት በነበረበት ጊዜና ከዚያም ብኋላ ) የዘር ማጥፋት እንዳይከሰት ለመከላከልየሚያስችሉ ያላቸዉን የደረጃ በደረጃ እርምጃዎችን እንደ

መፍትሄ ሀሳብ አቅርቦ ነበር:: እነዚህ የደረጃ በደረጃ እርምጃዎችም:-

1. ቡድኖች/ጎሳዎች/ብሄረሰቦች/የሀይማኖት ቡድኖች እኛና እነሱ በማለት የመከፋፈል ስነልቦና ላይ ሲደርሱ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል:: እርምጃዉም ሁል አቀፍ ተቋማትን በመፍጠር እኛና እነሱ የሚለዉን የስነልቦና አስተሳሰብ ማስቀረት ተገቢ መሆኑን ይመከራል::

2. በጥላቻ የተለወሰ ፍረጃ በስፋት በአንድ ቡድን/ማህበረሰብ/ብሄረሰብ/ጎሳ/የሀይማኖት ቡድን ላይ መለጠፍ ሲከሰት ለፍረጃነት ጥቅም ላይ የሚዉሉ ቃላት : ምልክቶችና ገለጻዎች በሙሉ በህግ መከልከል ይገባቸዋል:: እነዚህን የፍረጃ አስተሳሰቦች የሚያራምድ : በንግግር የሚገልጽ ሁሉ በህግ ሊቀጣ ይገባዋል::

3.አንዱ ቡድን የሌላዉን ቡድን ሰበአዊነት መካድ ላይ ሲደርስ አንዱ ቡድን አንዱን በነብሳት: በእንስሣት: በበሽታ መመሰል ደርጃ ላይ ይደርሳል:: ሲጠራዉም በዚሁ ሁኔታ ፓራሳይት: ደም መጣጭ: አዉሬ በማለት ይሆናል:: በዚህ ሰዓት የሀገ ዉስጥ መሪዎች : የአለም አቀፍ መሪዎች : የሀይማኖት አባቶች ይሄን አስተሳሰብ በግልጽና በገሃድ ሊያወግዙት ይገባል:: ጥላቻን በንግግር የሚያራምዱ ወገኖች ሁሉ ከአለም አቀፍ መድረኮች ሊገለሉና እንቅስቃሴያቸዉም ሊገታ ይገባል::

4.የዘር ማጥፋትን የሚፈጽሙት የተደራጁ (የራሳቸዉ ወታደር: አጥቂ ሀይል ያላቸዉ ) ቡድኖች ናቸዉ:: ስለሆነም የተባበሩት መንግስታትና የአለም ማህበረሰብ የመሳሪያ ግዥ ማዕቀብና ሌሎችም ተያያዥ ማዕቀቦችን ማድረግ አለበት:: አንዲት ሀገርም የዘር ማጥፋት ቡድኖችን አጥብቃ ትቆጣጠር ዘንድ የተባበሩት መንግስታት ሊያስገድዳት ይገባል::

5. የጥላቻ ቡድኖች ልዩነቶችን የሚያራግብ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ በሚያከናዉኑበት ወቅት አለም አቀፉ ማህበረሰብ ትኩረት ሊስጥና አክራሪዎች ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባዋል::

6.የጥቃት ሰለባ ቡድኖች በጎሳቸዉ/ በሀይማኖታቸዉ የተነሳ ሲገለሉ : ሲገፉ : ተነጥለዉ ኢላማ ሲሆኑ የዘር ማጥፋትን ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ እወጃ መደረግ አለበት::

7.የዘር ማጥፋቱን የሚፈጽሙ አካላት የሚያደርጉት ድርጊት የዘር ማጽዳት ስራ ወንጀል ነዉ ብለዉ አያምኑም:: ምክንያቱም እያጠፏቸዉ ያሉት ሰዎች ሰዉ ሳይሆኑ እንስሳትና ነብሳት ናቸዉ ብለዉ ስለሚያስቡ ሚያከናዉኑትን ግድያ ከሀይል በቀር የሚያስቆማቸዉ ነገር አይኖርም:: ስለሆነም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ ተጠቂዉን ቡድን ለማዳን ወታደሮቹን ማሰማራት ይጠበቅበታል:: እንዲሁም ተጠቂዎች የሚሸሹበት ነጻ አካባቢ ሊያቋቁም ይገባዋል::

8. የዘር ማጥፋት ወንጀሉን የፍጸሙ ሀይሎች የዘር ማጥፋት አልፈጸምንም በማለት ይክዳሉ:: የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዳላካሄዱም ወገባቸዉን ታጥቀዉ አይናቸዉን በጨዉ ታጥበዉ ሙግት ይገጥማሉ:: ለዚህ አይነቱ ክህደት ጠንካራ ቅጣት በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወይም በሀግሪቱ ፍርድ ቤት ሊወሰድባቸዉ ይገባል:: ሆኖም ሬጎርይ ከላይ መፍትሄ ብሎ ያቀረበዉን የደረጃ በደራጃ መፍትሄ ድሪክ ሞሰስ እና ሄለን ፌይ የማይጨበጥ ሲሉ ይተቹታል:: በተልይም ሄለን ፌይ እንደምትለዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚበቅለዉ በበርካታ መዋቅራዊ: ታሪካዊ: ባህላዊ: ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግብአቶች ላይ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ በደረጃ ደርጃ በሚወሰዱ እርምጃዎች የሚቀነበበ ጉዳይ አይሆንም:: ድሪክ ሞሰስም የርዋንዳን የዘር ማጥፋት ምሳሌ በማንሳት ይሄ ነገር እንዲህ ሬጎርይ እንዳለዉ የሚፈታ ቀላል ጉዳይ እንዳልሆነ የሬጎርይን ሀሳብ ይተቻል::

የሆነ ሆኖ አንዲት ሀገር የዚህ አይነት ጠንካራ ፈተና ዉስጥ ሊከታት የሚችሉ ምልክቶች በሚታዩበት ጊዜ ያገባኛል ባይ ወገን ሁሉ ስለጉዳዩ በቂ ንዛቤን መያዛቸዉና ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መዉሰዳቸዉ አለም አቀፉን ማህበረሰብ ከመጠበቅ የተሻለ ጉዳይ ነዉ ::

የአለም አቀፉ ማህበረሰብ በተለያዩ ትብት ፖለቲካዊ ፍላጎቶች የተወጣጠር ሀይል በመሆኑ : የተባበሩት መንግስታትም እዚህ ግባ የሚባል የመፍትሄ ሀይል ባለመሆኑ ቅድመ መፍትሄዉ መመንጨትና የዘር ማጥፋት ወንጀል በአንድ ሃገር ዉስጥ እንዳይከሰት አበክረዉ መስራት ያለባቸዉ የአንዲት ሀገር ልዩ ልዩ ሀይሎች ናቸዉ:: እነዚህ ሀይሎችም የሀገሪቱ ባለስልጣናት : የሀገሪቱ ተቃዋሚዎች: የሀገር ሽማግሌዎች: የሀይማኖት አባቶች: ተጠቂዉ እና አጥቂዉ ቡድን እራሱ እንዲሁም በሀገሪቱ ዉስጥ የሚገኙ የህግ ባለሞያዎች በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ መስራት አለባቸዉ::

የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዉም የሚጀምረዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ምልክቶች በሀገሪቱ ዉስጥ እየታዬ ነው ወይስ አይደለም የሚለዉን ጥያቄ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመፈተሸ ሁሉም ወገን ቀና ተንሳሽነት ሲያሳይ ነዉ:: ቀና ተነሳሽነት የሚባለዉም እኛና እነሱ ከሚል ጠባብ አመለካከት መዉጣት ሲቻል ብቻ ነዉ:: ዛሬ አጥቂ የመሰለዉ ወገን ነገ ተጠቂ ሊሆን እንደሚችልም በቂ ግንዛቤ በመያዝ ሁሉም ወገን ቅድመ መፍትሄዉ ለዚህ ወይም ለዚያኛዉ ቡድን ሳይሆን ለአጠቃላ ማህበረሰባዊ ደህንነትና ህላዌ መሆኑን ሊረዳዉ ከቻለ ብቻ ቅድመ መፍተሄ አሰሳዉ ዉጤታማ ይሆናል::

ሁኔታዎች ከቁጥጥር ዉጭ ከመዉጣታቸዉ በፊት ከራሱ ከሀገሩ የሚመነጩ መፍትሄዎችን ማበጀቱ ዋነኛ አማራጭ መሆን አለበት እንጅ ሬጎርይ እንደሚለዉ አለም አቀፍ ማህበረሰብ እስኪጫጫህበት ደርጃ የሚደርስ ነገር አለመኖሩን እርግጠኛ መሆን ይገባል:: የጥላቻ አስተሳሰቦች መሰረታዊ ባህሪያቸዉ ከአንዱ ወደ አንዱ መዛመታቸዉ ሲሆን ጥላቸዉ በሁለት ቡድኖች ብቻም ተወስኖ የሚቀር ጉዳይ አይሆንም::

ጥላቻዉ እንደ ሰደድ እሳት ሁሉንም የማያያዝ ባህሪ ስላለዉ ሁሉም ወገን ለራሱ እንዲሁም ወገኔ ስለሚለዉ ብሎም ለአጠቃላይ ማህበረሰባዊ ደህንነት ሲል በዚህ ነገር ጉዳይ በአንክሮ ቅድመ መፍትሄ ለማበጀት መንቀሳቀስ ተገቢ ነዉ:: ቅድመ መፍትሄዉ ሁሉ ከሀገሪቱ ከርሰ ማህጸን ዉስጥ አለ::

ዋናዉ ነገር በቅንነት ማወቅና የሁሉ ህላዌ በጋራ የተቆራኘ መሆኑን ተገንዝቦ ሁኔታዎች ወደ ባሰ ደረጃ ሳይራምዱ ቅድመ መፍትሄ ለማበጀት በጎ ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት ነዉ:: ለዚህም ሁሉም አካል ሀላፊነቱን ለመወጣት (መንግስት : ባለስልጣናት : ህዝቡ: የሀገር : ሽማግሌዎች: ተቃዋሚ ፓርቲዎች: የፍትህ አካላቱ እና ሌላዉም ወገን) ነገሮችን በቅንነት መገምገም ብሎም ቅድመ መፍትሄዎችን ማንሸራሸር ተገቢ ነዉ::